S.M.N.E

Solidarity Movement for a New Ethiopia

# ይታያችኋል? የኢትዮጵያ ሰማይ በብርሃን ተሞልቶ?

**ከአባንግ ሜቶ**

**December 24, 2008**

በመላ አለም ለምትገኙ እህቶችና ወንድሞች የከበረ ሰላምታ አቀርባለሁ የእየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች እንኳን ለልደት በአል አደረሳችሁ፤ እያልኩ አመት በአሉ የደስታ ጊዜ እንዲሆን እመኛለሁ፤ እየኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደው በቤተ መንግሥት ወይም በተንጣለለ ቪላ ሳይሆን በደሳሳ ጎጆ በምትገኝ ጋጥ ውስጥ ነው።

አንደዚሁም ለእስልምና ትከታዮች ወንድሞችና እህቶች አሰላም አሊኩም እያልኩ መጭው አመት የሰላም፤ የደህንነት፤ የተቀደሰና የተባረከ እንዲሆን እመኛለሁ።

ኢትዮጵያዊ የይሁድ ተከታዮች ለሆናችሁና በእስራኤልም ለምትኖሩ ደግሞ 'ሻለም ወይም ሰላም በመካከላችሁ ይሁን" ሀኑካ በሚከበርበት ፈጣሪ እግዚአብሄር ቅድስናውን ይለግሳችው፤ ሰላም ያስፍን መጭው አመት የተስተካከለ ኃይሉን እንዲለግሳችሁ እመኛለሁ።የሌሎች እምነት ተከታይ ለሆናችሁ ወይም ሌላ ምንም እምነት ለማትከተሉ ውድ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ይህ አመት የደስታና የመልካም ፍላጎት የሚሳካበትጊዜ እንዲሆን እመኛለሁ።

ኢትዮጵያ ሕዝቧ ቆንጆ፤ በተፈጥሮ የመሬት አቀማመጧ ደግሞ ውብ ሀገር ናት።ከቤተሰብ ጋር ሆናችሁ ይህንን የልደት በአልና አዲስ  አመት ስታከብሩ ትልቁን ቤተሰባችን ማሰቡን እንዳትረሱ። ኢትዮጵያ አንድ ቤተሰብ ናት። እድላቸው የጠበበባቸውን፤ በችግር ምክንያት የተራቡትን፤ ቤት የለሽ የሆኑትን በተለይም ደግሞ ከቤተሰብ ርቀው በኬንያ በስደት ጣቢያ የሚገኙትን፤ በመካከለኛው ምስራቅ በአስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ያሉትን እንደዚሁም በመንግሥት ቀጣይ ጫና ጥላቻ ስር አገር ቤት ሆነው ውሎ ማደር ፈተና የሆነባቸውንና በአካል የታሰሩትን  ወገኖች ሁሉ ይበልጥ እንድናስባቸው እጠይቃለሁ።

እዚህ ላይ ወታደር እንዲሆኑ የተገደዱ ወይም በማፍረስ ተግባር ላይ የተሰማሩና ከዚህ ችግር የመውጫ ዘዴውን ያላወቁትን የሕሊና እስረኞችን እንደዚሁ የእኛው ወገኖች በመሆናቸው ልንረሳቸው አይገባም።

ይህ ስነጽሁፍ በአጠቃላይ እነዚህን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። በእርግጥ በያንዳዳቸው ልቦና ውስጥ የሚያውጠነጥኑትን ጉዳይ ልናውቅ አንችልም። ነገር ግን የትብብር ንቅናቄ ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ አባላት ከተለያዩ ወገኖቻችን የሰማነውን ሀሳብ ግን እናካፍላችሁ፤ በተለይ ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በርካታ ኢትዮጵያውያን ስለንቅናቄው የሰጡት አስተያየት ሊያስደንቃችሁ ይችል ይሆናል። ለማንኛውም ባለፉት ሁለት አመታት በሽህዎች የሚቆጠሩ የስልክና የኢ-ሜል መልክት ደርሶኛል፡ እነዚህን የውስጥ ስሜትን የሚገልፁና ምንም እቀባ ሳይደረግባቸው በነፃ የተንሸራሸሩ ሀሳቦችን በማግኘቴ እድለኛ ነኝ፤ ምንም በቂ የሆነ ምስጋናየን የምገልጽበት ቃላት የሉኝም።

ይህ ከበድ ያለ ሥራ ነው። ነግር ግን የእናንተን ሀሳብ ማግኘት መቻል ታላቅ እድል ነው። በተለይም የበርካታ ኢትዮጵያውያን ስለ ንቅናቄው ያላቸውን ሀሳብ ማግኘት እጅግ ጠቃሚ ነው። በዚህ ረገድ ሁላችሁንም ለማዳረስ ባላመቻሌ በዚህ አጋጣሚ ሰላምታየ ለእናንተና ለቤተሰቦቻችሁ በሙሉ በያላችሁበት ይድረሳችሁ።

ሁላችሁም የሰጣችሁትን አስተያየት ከመበርከቱ የተነሳ ሁሉንም ላካፍላችሁ አልቻልሁም። ነገር ግን በተቻለኝ በተለያዩ ጽሁፎች በተከታታይ አቀርባለሁ። ከመጀመሪያዎቹ ሁለቱን በመላ አለም ከሚገኙ ኢትዮጵያውያን የተሰነዘሩ፤ ቀሪዎቹ ደግሞ ከኢትዮጵያውያን ውጭ ሆነው በጣም ቁልፍ በሆነ ደረጃ በአሜሪካ ምክር ቤትና በላዕላይ ምክር ቤት፤በአውሮፓ ፓርላማ፡ በካናዳ መንግሥትና በመሳሰሉት ቁልፍ በሆኑ የፓሊሲ አውጭ ኃላፊነቶች የሚገኙ ስለ ኢትዮጵያ የትብብር ንቅናቄ የሰጡትን ሀሳብ ነው የማካፍላችሁ።

እነዚህን ሀሳቦች አንድ ባንድ ሲደርሱኝ  የሚያስታውሰኝ በፅሎት ቦታ በትልቅ  የጨለማ አዳራሽ ውስጥ ያልበራ ሻማ ይዘው የሚገኙ የጸሎት ተካፋይ የሃይማኖት ሰዎችን ነው። ሻማውን አንዱ መጥቶ እስከሚለኩሰው ድረስ አዳራሹ በጨለማ እንአደተዋጠ ነው። በዚህ ወቅት ከጎን የተቀመጡትን ለመለየት እንኳን አዳጋች ነው።ሻማውን አንዱ ካቀጣጠለ በኋላ ግን አንዱ ላንዱ በቀስታ ያዳርሱታል ማን እንደሆኑም ለመተዋወቅ ቀላል ይሆናል። ይህ መጣጥፍም እንደዚሁ አይነቱን ሁኔታ ለማመልከት ነው። የሚጀምረውም በጡንቻ በክፍፍልና በመለያየት የተበከለን አዕምሮ በመዳሰስ ነው። አስተሳሰባችን ”ሰብአዊነትን ከብሄረሰብ” ቀደምትነት ባሻገር ነፃ ሆኖ አንዱ አንዱን በመረዳዳት ሁላችም ነፃ ካልሆን ማናችንም ነፃነት ሊኖረን አይችልም የተለያዩ ደረጃ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን መገንዘብ  ያለባቸው ይህንኑ ነው።

የኢትዮጵያውያን የተለያዩ አስተያየቶች ስታነቡ በጉዳዩ በጣም እንዳሰቡበት መረዳት ትችላላችሁ።ታዲያ ይህንን በትብብር ካዋሀድነው ከሀገራችን አልፎ ክፍለ አህጉሩን ሳይቀር  ሊያዳርስ ይችላል። አንድ ነገር ማስታወስ ያለብን በጨለማው ተጠቃሚ የሆኑት ክፍሎች መንጋቱንና ብርሃን መታየቱን አይወዱትም፤ ይቃወሙታል፤ ነገር ግን ማህበረሰቡ ከመሠረቱ መቀየር ሲጀምር ቢቃወሙትም ቅሉ ምንም ሊያደርጉት የማይችሉበት ደረጃ ይደርሳል። ይህ ሲሆን የወያኔን አባላት ጨምሮ በርካታዎች ወደ ንቅናቄው ይቀላቀሉ።

ሌላው የታህሳስ 3 ቀን በኢትዮጵያ በድጋሚ እንዲከሰት አልፈልግም። አንዳዶች የወያኔ ደጋፊዎችን ጨምሮ ለምን ለመላው ኢትዮጵያ ጥብቅና ቆምክ እያሉ ይጠይቁኛል። የእኔ መልስ በጋምቤላ የተፈፀመው ጭፍጨፋ በሌላው ኢትዮጵያዊ ጎሳ ላይ እንዲፈፀም ካለመፈለግ ነው።

ይገባኛል ይህ መንግሥት አጥንት የሚሰብር ጥላቻ በሕዝብ መካከል እየፈጠረ ነው። ይህ ችግር በብርቱ ጥንቃቄ ካልተያዘ በስተቀር አላስፈላጊ ወደ ሆነ መገዳደል ብሎም ሰቆቃን ሊያስከትል ይችላል። በመሆኑም ሌላ ታህሳስ 3 በኢትዮጵያ እንዲፈጠር አልፈልግም ያልኩት ለዚህ ነው። እርግጠኛ ነኝ ማንኛችንም ብንሆን ኢትዮጵያን ሌላዋ ሩዋንዳ እንድትሆን አንመኝም። አሁንም በብሄረሰብ ላይ የተመሠረተ ጥላቻ በተለያየ መልኩ ስር እየሰደደ ነው።

እዚህ ላይ ደስታ የተባለ የትግራይ ተወላጅ የነገርኝ ለብነት ያህል ላንሳ።ከ1997 ምርጫ ጋር በተያያዘ በወያኔ መንግስት የተፈፀመውን ግድያ በመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ ወጥቶ በሌሎች ኢትዮጵያውያን የመገለል ሁኔታ የተፈጠረበት መሆኑንና አንዳዶችም በግልጽ ይህ የወያኔ ወይም የትግራይ ሰላማዊ ስልፍ አለመሆኑን እንደ ነገሩት በዚህም ወያኔን ቢቃወመውም ቅሉ በሌሎች ወገኖችም የደረሰበት መገለል መሀል መንገድ ላይ እንዲያወላውል መገደዱን በመግልጽ ያደረበትን ቅሬታ ነግሮኛል።እንደዚህ አይነቱ በመደዳ ሁሉን መፈረጅ የንቅናቄአችን መሠረት መርህ የሚቃወመው ነው። በኢትዮጵያውያን መካከል ጥላቻን ለማፍራት የሚደረግን ሁሉንም ነገር እንቃወማለን። ይህ የጥላቻ መንገድ ሳይጎለምስ አሁኑኑ ልናኮስምነው ይገባል።

በቅርቡ በዋሽንግተን ዲሲ በተደረገ የቴዲ ይፈታ ስላማዊ ሰልፍ ላይ ከነበረው መፈክር አንዱ “ወያኔ ኢትዮጵያን ለቆ ይውጣ” የሚል ነበር በዚህ ረገድ በጀርመን  ሙኒክ ከሁለት አመት በፊት በተመሳሳይ ሰላማዊ ሰልፍ እናኑ የተባለች እህታችን የሰራችውን መጥቀስ እፈልጋለሁ። አንዱ በድምፅ ማጉያ “ወያኔ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ እንፈልጋለን” ሲል እናኑ ያለማወላወል ድምፅ ማጉያውን ተቀብላ “ወያኔ ከኢትዮጵያ እንዲወጣ ሳይሆን ከስልጣን እንዲወርድ ነው የምንሻው” በማለት አረመችው ወያኔዎች ኢትዮጵያን ለቀው የትም ሊሄዱ አይችሉም፤ሂዱ ቢባሉም መሄጃ የላቸውም ምክንያቱም የራሳችን ሰዎች ናቸው። ይህን መዘንጋት ተገቢ አይደለም። በቃላት አጠቃቀማችን ሳይቀር ጥንቃቄ ማድረግ ይገባናል። ምክንያቱም የጠላቶቻችን መንገድ በማጠናከር አላማችንን ያሰናክልብናል ።

ከዚሁ ጋር መረሳት የለለበት ጉዳይ ወያኔ /ኢሕአዴግ  ብዙዎችን ሰዎች  አባላት እንዲሆኑ እያስገደዳቸው ነው።አባል እንኳን ቢሆኑ ተጨባጭ ወንጀል እስካልሰሩ ድረስ መደዳውን መግፋት ላይ ጥንቃቄ ማድርግ ይኖርብናል። ሁሉም መለስን ይደግፋሉ ብሎ መደምደም እንዳይኖርብንና የኋላ ኋላ ጠቃሚ ወገኖች የሚወጣቸው ወገኖች እንደሚኖሩ ተስፋ እናደርጋለን።

እዚህ ላይ በሁሉም ብሄረሰብ ውስጥ ጥሩ የወያኔ ደጋፊዎች መኖራቸው ግልፅ ነው። በተቃራኒው በርካታ የትግራይ ተወላጆች መለስን ይቃወማሉ። በመሆኑም ሁሉንም የሚመዝነው ሥራ እንጂ ብሄረሰብ መሆን የለበትም። እንደኔ እምነት መለስ ለትግሬዎች ጉዳይ ያለው አይመስለኝም፤ እንዲያውም እንደእኔ እምነት መለስና ግብረበሎቹ በትግራይ ስም ስልጣን ለማቆየት ያለአግባብ የትግራይ ተወላጆችን እየተጠቀሙባቸ ነው። የእነመለስ ፓሊሲ መጀመሪያ “ለእኔ ነው” የትግራይ ተወላጅ ሁኖ የመለስ ሎሌ ካልሆነ እንደሌላው ይጣላል። ተመልከቱ ድሀ የትግራይ ብሄረሰብ ተወላጆችን በአዲስ አበባ ጎዳና በልመና ተሰማርተዋል። መለስ ምን ሠራላቸው? መለስን የሚቃወሙ ስንት የትግራይ ልጆች ሰብአዊ መብታቸው ተጥሷል።

አኝዋኮች ተጨፈጨፉ ገዳዬቹ እስካሁን ለፍርድ አልቀረቡም። እኔ እነዚህን ሰዎች በጥላቻ አላያቸውም በተቃራኒው እወዳቸዋለሁ። ምክንያቱም ጥላቻ ይበልጥ ጥላቻን ነው የሚወልደው ብየ ስለማምን እንጂ ለፈጸሙትን ድርጊት ግንባር ቀደም ተቃዋሚ ነኝ ማንኛችንም ብንሆን በጥላቻ ላይ የተመሰረተ ኑሮን አንሻም።

በተቃራኒው የትብብር ንቅናቄ የሚሻው  ሁሉንም ኢትዮጵያውያን ያቀፈና  መሠረት ያድረገ አዲስ ኢትዮጵያ እንሻለን ከሰሜን፤ ከኦሮሞ፤ ከኦጋዴን፤ ከአፋር ከቤንሻንጉል- ጉምዝ፤ ከአማራ ክልል፤ከደቡብ ፤ከጋምቤላ፤ ከሐረር፤ ከክርሲቲያን ከእስላም፤ ከሴቶች ከወንዶች፤ከእድሜ ስብጥር ከተለያዩ የፓለቲካ እምነት ተከታዩች ማናቸውም ማሕበረሰብ የሚወክሉት በግለስብ ደረጃ እራሳቸውንና አመለካከታቸውን ብቻ በዝርዝር ያስረዳሉ የተወሰነውን እነሆ፤

ከቶረንቶ ካናዳ የትግራይ ተወላጅ የሆነ ግለሰብ በቅዲሚያ ኢትዮጵያዊ ነኝ ከዚያም የተወለድኩት ትግራይ ነው፤ ባለትዳርና የልጆች አባት ነኝ፤ ልጆቼን የማስተምራቸው ሀገራቸውን እንዲያውቁ ነው፤ የት እንደመጡና ባህሉን ጨምሬ ለማስተማር የበኩሌን በቤተሰብ ሀላፊነቴ እየጣርኩ ነው። የጨነቀኝ ግን ወያኔ በትግራይ ሕዝብ ስም እየፈፀመ ያለው ተግባር እጅግ ጎጂ ነው። እኔ በሁለት ባላ ላይ ቆሜ ተቸግሬአለሁ ካለ በኃላ፤ የወያኔ ደጋፊ አይደለሁም።  ግን በዚህ በትግራይ ተወላጅነቴ አብረው ይደምሩኛል። ለምሳሌ በ1997 ምርጫን ተከትሎ በተፈፀመው ግድያ ተቃውሜ ከሌሎች የቶሮንቶ ነዋሪ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር ሰላማዊ ስልፍ ብወጣ ይኸ እኮ የወያኔ ስላማዊ ስልፍ አይደለም በማለት አንዳንድ ስልፈኞች አሸማቀቁኝ። ለእኔ ይህ ንቅናቄ በወጣው መርህ የሚገዛ ከሆነ የኢትዮጵያን ሕዝብ ግልፅነት፤ ነፃነት እና የማህበረሰቡን መቀራረብና እርቅ ሊያመጣ የሚችል መርህ ነው በመሆኑም ወድጀዋለሁ ይላሉ።

የኦጋዴን ነፃ አውጭ ግንባር መሪ ከአሜሪካ ሚኒሶታ ደግሞ የትብብር ንቅናቄ ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ መርህ ድርጅቴ ከሚታገልለት አንዱ ነው። በመሆኑም በኢትዮጵያ ይህ መርህ ተግባራዊ የሚሆን ከሆነ ኦነአግ ከኢትዮጵያ ጋር አብሮ ለመኖር የማይችልበት ምክንያት የለም ሲሉ ቃላቸውን ሰጥተዋል።

ከአዲስ አበባ አቶ ባልቻ በበኩላቸ ደግሞ የ1997 ምርጫን አስመልክቶ ሰላማዊ ሰልፍ ከወጣነው በሚሊዮን ከሚቆጠሩ ወገኖች አንዱ እኔ ነኝ። የእኔን መሰሎች ትናንትም ነበርን አሁንም ከዚያው አለን። ያጣነው ነገር ቢኖር አመራርና ድርጅት ነው።ሀገሪቱን ነፃ ለያወጣ የሚችል ሁኔታ ሲመጣ ፤ያ ጥሪ በቀረበ ጊዜ፤እና አመራር ሲገኝ አሁንም ጥሪውን ተግባራዊ ለማድረግ መልስ እንሰጣለን። ከካሊፎርኒያ ኦክላንድ ጺዮን ስለ አንተ /ኦባንግ ሜቶ/ አዲስ ነገር እየተማርኩ ነው። በተግባር ላይ የምታተኩር ሰው ነህ። አሁንም የምነግርህ በዘዴ፤ በስልት፤ በቀጣይነት እና በተቀነባበረ እቅድ ለመሥራት ከቻልን እንደሚሳካልን ላረጋግጥልህ እወዳለሁ፤

የለንደኑ ነዋሪና የሙርሲ ብሄረሰብ ተወላጅ ሄኖክ ደግሞ የትብብር ንቅናቄውን ለአዲስቲ ኢትዮጵያ ከሁሉ ያስደነቀኝ መርሁ ሁሉን አቀፍ መሆኑ ነው ካለ በኋላ ከፓለቲካ ስልጣን ይልቅ ለሰው ልጅ ክብርና ሰብእና መታገል ትልቅ ነገር ነው። ምእራባዊያን ሙርሲ ወጥተው የሚያደርጉት ነገር ቢኖር ሴቶቻችን በከንፈራቸው ለጌጥ የሚያንጠለጥሉትን ሸክላ ፎቶ አንስተው መሄድ ብቻ ነው። ሕዝባችን ንፁህ መጠጥ ውኃ፤ የትምህርት እድል እንዲያገኝ አይረዱም ቢያንስ እንደ ማእከላዊ ሀገር ማለት ነው፡ እኔ እራሴ ትምህርት ያገኘሁት በሀይማኖት አማካኝነት ነው።

ከአዲስ አበባ  የሸንጎ አባል በበኩላቸው ትብብሩ ተጠናከሮ መቀጠል ያለበት ጉዳይ ነው ካሉ በኋላ እኔ ኢትዮጵያውያንን የምጠይቀው ንቅናቄውን ሕዝቡ እንዲቀላቀለው ነው። የትብብር ንቅናቄው የውጭውን ካስተባበረ የአገር ቤቱ ሕዝብ በቀላሉ ይዳረሳል የሚል ግምት ቢኖረኝም ቅሉ የውጭውን ለማዳረስ እንደሚያስፈልገው ሁሉ በአገር ቤትም በጣም ተፈላጊ የሆኑ ሥራዎችን ማከናወን ይጠበቅበል። ለዚህም ነው ከተለያዩ ፓለቲካ ድርጅቶች፤ከተለያዩ ክልሎች፤ከተለያዩ የብሄረሰብ ክፍሎች የተሰባሰቡትና የዴሞክራሲ ፎርም  የተመሠረተው ተስፋ የምናደርገው  የትብብር ንቅናቄው ይመራናል ብለን ነው ።

የለንደን ነዋሪውና የሻኪቾ ብሄረሰብ ተወላጁ አቻም የበኩሉን ሀሳብ እንዲህ በማለት ነው ያብራራው "ሊጠቅመን በሚችል ጉዳይ ላይ ኢትዮጵያዊያንን ማስተባበር አስፈላጊ ነው። መከፋፈል ሁላችንም ጎድቶናል። መንግሥት ሕዝቡን ከፋፈለ እርስ በእርሳችን በጠላትነት እንድንተያይ አደረገ የትብብር ንቅናቄውን መርህ የወደድኩት ከመከፋፈል ሕዝዝቡን በአንድ ላይ ማሰባሰብ ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው።ስለሆነም ሕዝብን ከአንድ ላይ የሚያሰባስብ ነገር ላይ ለመተባበር ዝግጁ ነኝ።

ሙሉጌታ ከአዋሳ በበኩሉ ለለውጥ እንነሳ ሲል የተመራጭ አባማን ተምሳሌት ጠቅሶአል። ከጀርመርን ፍራንክፈርት የአፋር ነፃ አውጭ ግንባር አባል አብዲፋታህ በሰጠው አስተያየት ከትብብር ንቅናቄ አላማ ጋር እስማማለሁ ካለ በኋላ ይህ መርህ ለአፋር ሕዝብ እንደቀረበ ጥሪ ነው የማየው በማለት ድጋፉን በመግለጽ ለአፋር ሕዝብ የልማት እድል አልተሰጠውም በመሆኑም ይህንን ጉዳይ ለማስፈፀም በመንቀሳቀስ ላይ ነን በተለይ ሁላችንም ነፃ ካልወጣን ማንም ነፃ አይወጣም ማለት ሁሉንም የሚያጠቃልል  ጉዳይ በመሆኑ የጉዞው ተካፋይ ነን ብሏል።

ለምለም ከቫንኮቨር ካናዳ ደግሞ ለምታደርገው ጥሪ ያለኝን አድናቆት ልገልጽልህ እፈልጋለሁ። ይህ ጥሩ ታላቅ ጥሪ ነው። ያንተን ጥሪ በጣም እደግፋለሁ አንድ ነገር ማድረግ አለብን በአንድ ድምፅ መምጣት ይኖርብናል። አገዛዙ ባለመተባበራችንና በድክመታችን የተነሳ እንደፈለገ ብሄራዊ ክብራችን እና ሕዝባችን ያጠቃል በመሆኑም የሕዝባችን ብሶት እስከሚወገድ በጋራ እንነሳ ስትል አስረድታለች።

ከኦሞ ሸለቆ የመጣው ጃቆብ ከኦትዋ "የንቅናቄው መርህ ስለእኔ ነው የሚናገረው ይህ መርህ ተግባራዊ ከሆነ ወደ 21ኛ ክፍለ ዘመን በአንድነት ያሸጋግረናል። የእኔ ትውልድም ሆነ ሕዝብም ይጠቀማል" ሲል የአኝዋክ ፓስተር ከጋምቤላ ደግሞ የንቅናቄው መርህ በጣም አስፈላጊ ነው እውነትን ይናገራል፤ እውነትን ያስተምራል፤ ለአውነት ቁሟል በመሆኑም ኢትዮጵያ የምትሻው ይህንኑ ነው በማዕከላዊ ሀገር የተወለደና በጋምቤላ ያደገ የጋምቤላ ቋንቋ የሚናገርና ለወያኔዎች የወገነ ግለሰብ በታኅሳሥ ወር ላይ ሶስት የጋምቤላ ተወላጆችን ገሏል። እግዜብሄርን ቢፈራና ለእውነት ቢቆም ኑሮ ይህን አይፈፅምም ነበር። የትብብር ንቅናቄውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከደገፈው የአፍሪካ ብሄራዊ ኮንግረስ አይነት የእርቅንና የእውነት መንፈስ ያመጣል የሚል እምነት አለኝ ብሎአል።

እንደዚሁም ከለንድን አንድ ኢትዮጵያዊ በሰጡት አስተያየት የተብብር ንቅናቄ መርሆዎች እውነትና ተስፋ የተላበሱ ናቸው ይህ ነው ሰብእናንና ሰብአዊነትን መጠበቅ ካሉ በኋላ በተማሪዎች ንቅናቄ ወቅት ኢትዮጵያ ነበርኩ ንቅናቄው አንዱ አንዱን የሚጠብቅበት ሳይሆን አንዱ አንንዱን የሚያጠፋበት ነበር በዚህ ንቅናቄ የተነሳ 30,000 የሚሆን ሕዝብ ሕይወት መጥፋቱን በቁጭት ካአስታወሱ  በኋላ  የሁለቱ ንቅናቄዎች ያላቸው ልዩነት በማነጻጸር የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ንቅናቄ ለሰው ሕይወት ዋጋ የሚሰጥ በመሆኑ እደግፈዋለሁ ብለዋል። ከጀርመን የዶክትሬት ድግሪውን በመማር ላይ ያለው አዳነ በፊናው በቅድሚያ የኢትዮጵያን የመጭ እድል ለመቅረጽ ላደረከው ጥረት ላመሰግንህ እፈልጋለሁ፤ በንቅናቄው መርህ ላይ ሁሉም ጉዳዮች ተካተዋል።ይህን ካልኩ በኋላ እራሴን እንዳስተዋውቅ እፈልጋለሁ። በመታደል ወይንም ያጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ ከትግራይ፤ከአፋርና ከሶማሌ ክልሎች በስተቀር ሌላውን የኢትዮጵያ ክፍል በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ስሠራ አውቀዋለሁ።ሁሉም ገጠር ሕዝብ ጎጃም ፤ጎንደር ፤ቤንሻጉል -ጉሙዝ ወይም ጋምቤላ ፤ኦሮሚያ ወይም ደቡብ ሕዝቦች ሁሉም የሰቆቃ ኑሮ የሚገፉ ናቸው።በመንግስት እንደዜጋ የሚቆጠሩ አይደሉም።የሁለተና ደረጃ የዜግነት እድሉ እንኳን የላቸውም።ይህን ስል የከተማው ሕይወት የተሻለ ነው ለማለት አይደለም።ብዙሀኑን ለመጥቀስ ያህል ብቻ ነው።

በ1997 ምርጫ ወቅት ሀገር ቤት ነበርኩ።የሕዝቡ ተሳትፎው አስደናቂ ነበር።ብሩህ ተስፋ በሁሉም ታይቶ ነበር አሁን ግን ወደ ድሮው እየተመለሰ ነው ።ወያኔ መቀመጫውን አደላደለ፤ እማማ ኢትዮጵያ ግን እየተሰቃየች ነው። በመሆኑም ትግላችን እንዲጠናከር ከገናችሁ ነኝ ብሏል።

እንደዚሁም በአሜሪካ የሎስ አንጀለስ ነዋሪ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ቄስ፤ አሞት ከጋምቤላ፤ የጎጂ ተወላጅ ከሎስ አንጀለስ፤ የሕክምና ዶክተር ከቼዝ ረፐብሊክ፤ ዳምጠው የተበላ የአለማቀፍ ግንኙነት ተማሪ ከሲውዘርላንድ፤ የኦጋዴን ተወላጅ ሳዲቅ፤ ከሀዲያ ወልዴ፤ ትዝታ ከአሜሪካ የሚንሶታ ኤርፓርት ሰራተኛ፤ የምስራች ከቴላቪቭ ዩኒቨርስቲ እንደዚሁም የኢሕአዴግ መንግስት ባለልጣን ከአትዮጵያ፤ አቶ በላይ በእንግሊዝ ለንደን የባንክ ሰራተኛ፡ አብዱራሂማን የእስልምና ሀይማኖት ኢማም ከቶሮንቶ፤ ፕሮፌሰር ሰይድ  ከአሜሪካ ኬንታኪ የተለያዩ የደጋፍ አስተያየቶችን ለንቅናቄው መርህ ሰጥተዋል።

በተለይ ዶ/ር ጎልቶ ከአሜሪካ ሰፋ ያለ አስተያየት የሰጠ ሲሆን አስተያየቱ ያተኮተው አባንግ በጉርጅና በቡርጅ መካከል ተነስቶ ስለነበረው ግጭት ያደረገውን ጥረት በምሳሌ በመጥቀስ ነበር።እንዲህም ይላል፤ ስለግጭቱ ለአባንግ ስደውልለት ሁለቱንም ብሄረሰቦች አያውቃቸውም፡ ስለሁኔታው ከገለጽኩለት በኋላ ግን በአኘዋክ ላይ የተፈፀመው ሰቆቃ በማስታወስ ወዲያው ወደ ተግባር ተሰማራ፤በመቀጠልም አምስት የተለያዩ ሀገራት የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤቶችን የአሜሪካንና ካናዳን ጨምሮ ደውሎ ጉዳዩን አሳሳቢነት አስረዳ፤  በመቀጠልም ወደ ሂዩማን ራይት ወች ፤ የጅምላ ጭፍጨፋ ተመልካች ቢሮ እና ወደ በርካታ መ/ቤቶች ጉዳዩን አመለከተ ብዙዎች የመለሰን ቢሮ መጠየቃቸዉንና ጉዳዩን በመከታተል ላይ መሆናቸውን በመግለፅ መልስ ሰጡ። ይህ እንደተሰማም ግጭቱ ረገበ። በትክክል የጦርነቱን አፈመዝ አንዲቆም ማን እንዳዘዘና እንዲቆም እንዳደረገ ባናውቅም አንድ የወያኔ ባለስልጣን ግን ትእዛዝ መሰጠቱን ማወቅ ችለናል የአባንግ ጩኸት መልክት ማስተላለፉም ግልጽ ነበር።

ብዙዎቹ የተቃማዊ ፓለቲካ ድርጅቶች የሚኖሩት ለራሳቸው ፈላጎት ነው አንድም የፓለታካ ድርጅት በረሀብ ለሚሰቃዩና በሚሊዮኖች ቁጥር ላላቸው ወገኖቻችን የገንዘብ መውጮ ሲያስተባብር ሰምቸ አላውቅም እንደዚሁም መሪዎች ሕዝባችንን ከማቀራረብ ይልቅ የመራራቅ ተግባር ነው የሚፈጽሙት፡ ሆኖም ከደቡብ ኢትዮጵያ የመጣው አባንግ የኢትዮጵያውያን ችግር ገብቶት እየጮኸ ነው አባንግ ሜቶ ስለትብብር ይለምናል፤ ይሰብካል፤ ይፀልያል ስለዚህ የሚፈልገው ከጎኑ እንድንቆም ነው። ለሁሉም የወያኔ ስለባ ለሆነ የጉርጂ ተወላጆች ግልፅ ማድረግ የምሻው ቦረናን፤ ገብራን፤ ጋሪን፤ ሲዳማን፤ ኮራንና ሊሎቹንም ጨመሩበት በመሳሪያነት ወያኔዎች ተጠቀሙባቸው ይህም የታወቀው የከፋፈለህ ግዛው መርህ መሆኑን ነው።

መለስ የተሳሳተ አገዛዙን እንዳንታገል የግጭት አካባቢ ፈጠረልን። ብሄረሰቦች እርስ በእራሳችን እንድንጋጭና ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ ሲወጡ ሕግ አስከባሪ መስሎ ይቀርባል። አሁን የመለስ መሳሪያ የሆኑት ጉጅዎች ምን አይነት ሕይወት ወደፊት  ሊኖሩ ነው?  ይህ ቀን ተመልሶ ወደ እነርሱ እንዳይዞር እየተጠባበቁ ነው። ይህ ነው የሚያሰጋኝ። ይህ አይነት መበቃቀል መላ ኢትዮጵያን ይለበልባል፤ ስለሆነም የአሁኑ ትምህርት ሆኖን ሁላችንም ለምን በአንድነት ተነስተን ይህንን የጥፋት ድግስ እናጨናግፈው። ይህን ስል ጉጂና ቡርጂ ሳይቀሩ ማለቴ ነው። አሁን ያለውን መከፋፈል የሚያቆመው ወገናዊ ያልሆነና ከፓለቲካ የራቀ ትብብር ብቻ ነው። ይህ አንድነትን የሚያመጣ ስለሆነም ይህ የተብብር ንቅናቄ እናት ሀገራችን ያድናታል፤ አንድ ላይ ያገናኝናል አሁንም እንቅሳቀስ ብዙ አወራን ወደ ተግባር እንሸጋገር።

ቢኒያም የትግራይ ተወላጅ ከማኒሶታ፤ የቀድሞው የሕወሀት ባለስልጣን ከኢትዮጵያ፤ አልማዝ ከቨርጂንያ፤ ከቻይና ኢትዮጵያው ነጋዴ፤ አምልማል ከቦስተን፤ ፕሮፌሰር  ማሞ መጨ ከዴንማራክ፤ ግርማ ከአሜሪካ፤ ኢብራሂም በቤንሻጎል-ጉሙዝ፤ ደረጃ ከወላይታ፤ አብቲ የጌዲዮ ብሄረሰብ አባል የየበኩላቸውን የድጋፍ አስተያየት ሰንዝረዋል።

በተለይ አንድ የወታደራዊ አዛዥ ከኢትዮጵያ በመጀመሪያ በትብብር ንቅናቄ መርህ ላይ እስማማለሁ ካሉ በኋላ አንዳንዶች የወያኔ ወታደሮች ይሉናል እኛ የኢትዮጵያ ወታደሮች ነን። ሀገራችን እንዳትጠፋ የምንታገል፤ የሕዝባችን መገደል የምንቃወም፤ስንሆን   ድምጻችን የማትሰሙበት ምክንያት በርካታዎች ከበው ይከታተሉናል ብንናገር የትም ወስደው እንደሰው ሳይሆን ልክ  እንደዝንብ የገሉኛል። በርካታ የኢትዮጵያ ወታደሮች ለለውጥ የተዘጋጁ አሉ ግን ድምጻቸው የሚሰማበት  ሁኔታ የለም ይህንን ለመግለፅ መንገዱ ሁሉ ዝግ ነው።

ብዙዎቻችን ለለውጥ ድምጽ ሰጥተናል።እኔ ለቅንጅት ድምጼን ሰጥቻለሁ። አማራጭም አልነበረኝም፤ ብዙዎቻችን ጊዜው ሲመቻች ተዘጋጅተን የምንጠብቅ መሆኑን እወቁት ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ዮናታን ከሜልቦርን አውስትራሊያ በሽር፤ መስከረም፤ ገዚ ከአሜሪካ ማህሌት ከደብረብርሃን፤ የኒዮር ብሄረሰብ ተወላጅ ከካልጋሪ፤ ከአትላንታ አንድ የፕሮቲስታት ኢትዮጵያዊ ፓስተር፤ ተሰማና ቤላ ከዩኤስ ኤ ተመሰሳይ የሆነ የድጋፍ አስተያየት ሰጥተዋል።

ማጠቃለያ የእነዚህን ሰዎች አስተያይት እንኳ ብተመለከቱ ከተለያዩ የሕብረተሰባችን ክፍል የተወጣጡ ናቸው። ነገር ግን አንድ  ነገር በጋራ አላቸው ይኸውም ማንም ከሕግ በላይ ያልሆነበት፤ ሰላም፤ ፍትህና የሁሉም የተሳተፎና የተጠቃሚነት ተስፋ በእኩልነትና በነፃነት ላይ የተመሠረተች ኢትዮጵያ ናት። ይህ ከላይ ለመግለፅ የተሞከረው ከደረሱን አስተያየቶች መካከል እጅግ በጣም ጥቂቱን በመምረጥ የቀረበው። እድሉ ሰፋ ብሎ ከተገኘ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሀሳባቸውን ለመግለፅ ዝግጁ ናቸው።

አሁን ሁላችሁንም የምንጋብዘው የቡና ተርቲም ውስጥ አብራችሁ እንድትጠጡ ነው። ቡና ከጎረቤት ሲጠራ ማንም አይቀርም፤ ሁሉም ተሳታፊ ነው ስለሆነም የቡናው ተርቲመኞች ሁሉም በአንድ ጀበና የፈላ ቡና ነው የሚጠጡት።

የጀበና ምስል ምን እንደሚመስል የታወቀ ነው አሁን ይህን ምስል በአምሮአችሁ አስቀምጣችሁ የኢትዮጵያን ካርታ ተመልከቱ ተመሳሳይ ነገር ይታያችኃል? ካልሆነ ትንሽ ላብራራው በአጋጣሚ  በቅርብ ይህንን የሁለቱን ቅርፅ ተመሳሳይነት ሳይ በጣም ደነቀኝ። የኢትዮጵያ ቅርፅና ጀበናውን አስተያዩት።የጀበናውን መያዥ ብትመለከቱ የጋምቤላን ክልል ያመለክታል በሌላ በኩል ደግሞ ያለው አጋዴንን ያሳያል ጭንቅላቱ ኤርትራን ያመለክታል፤ ዋና የጀበናው አካል ማእከላዊንና ቀሪውን የሀገሪቱን ክፍል ያካትታል።

ኢትዮጵያ ቡና የተገኘባት ሀገር መሆኗ ይታወቃል። ሁላችንም ቡና  ምን ማለት እንደሆነም እናውቃለን። በተለይ ቡና በምንጠጣበት ወቅት ከሌሎች የተቀደሱ ባህሎቻችን በተለይ ምን ያህል እንግዳ ተቀባይ መሆናችን መከባበርና መፈቃቀርን የሚያመለክት ነው።

ቡና አፍይዋ ጀበናውን በጣም በጥንቃቄ ነው የምትይዘው ጀበናው በእንዝህላልነት ከወደቀ ይሰበራል ቡና ጠጭዎችም ይበተናሉ ይህ እንዳይሆን ነው የቅድሚያ ጥንቃቄው የሚያስፈልገው። ኢትዮጵያም ዛሬ የብሄረሰብ ፓለቲካው በጥላቻ፤ በምዝበራ፤ በማታለል፤ በስግብግብነት፤ በጠመንጃና በጭካኔ የተያዘ ነው።ይህን ሁኔታ በጥንቃቄ ካልተያዘ ሀገሪቱን ሊበታትናት ይችላል። በዚህ ወቅት ተጠቃሚው ማን ነው? ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ በጋራ በአንድ ላይ ካልቆመ አሁን በጀበና መልክ የምናያት ኢትዮጵያ ገጽታዋ እየተቀየረ ነው። ይህን በኤርትራ መገንጠል ተመልክተናል። የጀበናው ቅርፅ ኤርትራ ካልጨመረ እርሱም የለም ጋምቤላ በጀበናው እጅ ላይ ነው ያለው። አጋዴን ደግሞ በሆድ እቃው ጫፍ ላይ ነው ያረፈው ይኸውም ብዙ  የኢትዮጵያ ግዛቶችን የያዘ አካል ነው። ይህ የብሄራዊ ጥቅማችን ነው የእያንዳዳችንም ድርሻ ነው። በመሆኑም የወደፊቱን ኢትዮጵያን ለመጠበቅ አንድ ላይ እንሰባሰብ።

አሁን በሰብአዊ መብት ጥሰት የምትታወቅ ኢትዮጵያን ሳይሆን የጠነከረና ሰብ አዊነት የተላበሰች ኢትዮጵያን በጋራ እንድንገነባ የትብብር ንቅናቄ ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ አባል እንድትሆኑ ትጋብዛችኋል። ይህ ጥሪ ለነፃነትና ለመገንጠል የሚፈልጉትን ቡድኖች ጭምር የሚያጠቃልል ነው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው የኢትዮጵያ ካርታ፤ የኢትዮጵያ ስም እና ሰንደቅ አላማዋ ማንንም ብሄረሰብ አልጨቆነም፤ አልገደለም፤ ሁል ጊዜም በመንግስት ውስጥ ያሉ ግለሰቦች ናቸው ይህንን የፈፀሙት። በመሆኑም ልክ ቡና በጋራ ተሰባስበው እንደሚጠጡ ተርቲመኞች ለሁሉም ተገቢ ቦታ ከተፈጠረ መገንጠል አያስፈልግም።

በጋራና በጥንቃቄ የሀገራችን ፓለቲካ ልንይዘው ይገባል። ፍቅርን፤ እውነትን፤የሀላፊነት ስሜትን ሰላምን፤ ፍትህን እና እኩልነትን በመላ ሀገሪቱ ማዕዘናት የጨለመው ብርሃን እስከሚስጥ ድረስ መታገል አለብን።

እግዘአብሄር ምን አልባት በእነዚህ መርሆወች ወይም በሌላ ምክንያት መልካም ፈቃዱ ሆኖ በቅርብም በሩቅም ያለን በፍቅርና በሰላም ሁሉን ያቀፈ ደስታ ተካፋይ ልንሆን እንችላለን። ከጥላቻ ይልቅ ለፍቅር ከፍትህ መጎደል ፍትህ የሰፈነበት ከአድልወ ወደ እኩልነት ለመሸጋገር ቆርጠን ከተነሳን እንችላለን።

ደስታና ፍቅር እግዘብሄር ይለግሰን እያንዳዳችንም ይህንን መልክት ኢትዮጵያ ውስጥ ላሉ፤ ለአፍሪካ ቀንድ ብሎም ለመላው አፍሪካ እናስተላልፍ ከሁሉ በላይ ግን እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይቀድሳት።

አስተያየት ለመስጠት የምትፈልጉ  በዚህ አሜል ተጠቀሙ

================================

Please do not hesitate to email your comments to me at: obang@anuakjustice.org